የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# ኦንላይን የመራጮች ምዝገባ ስርዓት መምሪያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኦንላይን የመራጮች ምዝገባ ስርዓትን የዘረጋው የመራጮች ምዝገባ በሚካሄድበት ወቅት የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ፣ ነገር ግን በድምፅ መስጫ ዕለት የትምህርት ዘመኑ መጨረሻ ስለሚሆን ድምፃቸውን በቋሚ መኖሪያቸው (የመኖሪያ አድራሻቸው) ለሚሰጡ ተማሪዎች የመራጮች ምዝገባ እንዲካሄድ ለማስቻል ነው።

አንድ ተማሪ በኦንላይን ለመመዝገብ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለበት፡

- የኢንተርኔት አገልግሎት መኖር አለበት
- ላፕቶፕ ወይም ሞባይል ስልክ ሊኖር ይገባል
- የመራጮችን ምዝገባ ለማጠናቀቅ መጫን ያለበትን የተማሪ መታወቂያ ካርድ ስካን አድርጎ ማዘጋጀት አለበት
- በቋሚነት በሚኖርበት አድራሻው መሰረት ድምፅ ለመስጠት የሚመዘገብበትን የምርጫ ጣቢያ ስም ማወቅ አለበት። የሁሉንም የምርጫ ጣቢያዎች ስም ከዚህ ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡ www.nebe.org.et. ተማሪው ከቋሚ የመኖሪያ አድራሻው አቅራቢያ የሚገኘው የምርጫ ጣቢያ ስምን በተመለከተ እርግጠኛ ካልሆነ፣ ለምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ጽ/ቤት፣ ለቤተሰቦቹና ለጎረቤቶች ጥያቄ አቅርቦ መረዳት ይችላል።

በኦንላይን የመራጮች ምዝገባ ሒደቶች

ተጠቃሚዎች በመጀመሪያ የኢንተርኔት ኮኔክሽን ባለው ኮምፒዩተር ወይም ሞባይል ስልክ በዚህ አድራሻ www.ovrs.gov.et ወይም በ www.nebe.org.et በመግባት ሲስተሙን መክፈት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቋንቋንም መቀየር ያስችላል። በመቀጠልም ወደ አዲስ የተማሪ ምዝገባን ሊንክ መንካት




ደረጃ 1 – የተጠቃሚ መለያ (አካውንት) መፍጠር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

የኦንላይን የመራጮች ምዝገባ ስርዓት (www.nebe.org.et) ላይ ገብተው የሚከተሉትን መረጃዎች በማስገባት የተጠቃሚ መለያ (አካውንት) መፍጠር ይችላሉ፡

- ሙሉ ስም እስከ አያት
- ተማሪው የሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ስም
- የተማሪ መታወቂያ ካርድ ቁጥር
- የስልክ ቁጥር
- የኢሜይል አድራሻ
- የይለፍ ቃል ይፍጠሩ






ደረጃ 2 – የመለያ (አካውንት) ትክክለኛነት ማረጋገጫ

አካውንቱ በስርዓቱ ላይ አንዴ ከተፈጠረ፣ የአካውንቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ማስፈንጠሪያ (ሊንክ) የያዘ ኢሜይል እርስዎ አካውንቱን በከፈቱበት የኢሜይል አድራሻ በኩል ይላክልዎታል።

የአካውንቱን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና የመራጮች ምዝገባ ገጽን በመክፈት የግል መረጃዎችን ለማስገባት የማረጋገጫ ማስፈንጠሪያውን ጠቅ ያድርጉ።




ማስፈንጠሪያውን ከነኩት በኋላ የሚከተለውን ገፅ ያገኛሉ




**<u>የይለፍ ቃልዎን በማስታወሻ ጽፈው በጥንቃቄ ማስቀመጥዎን ያረጋግጡ፤ በሌላ ጊዜ ወደ አካውንቱ በመግባት የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማተም ይህ መረጃ ያስፈልግዎታል።</u>**

ደረጃ 3 – የግል መረጃ ማስገባት

የተጠቃሚው አካውንት አንዴ ከተከፈተና ከተረጋገጠ በኋላ፣ ተማሪው፡

- ዕድሜውን ያስገባል
- ፆታ ይመርጣል

- ○ የቋሚ መኖሪያውን ሙሉ አድራሻ ያስገባል (ክልል፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ መንደር/ጎጥ፣ የቤት ቁጥር)
- ○ በምርጫ ክልሉ ውስጥ የኖረበትን ጊዜ ያስገባል (ዓመታትና ወራት)

ተማሪው ባስገባው ቋሚ መኖሪያ አድራሻ መሰረት፣ ስርዓቱ ተማሪው ድምፅ ለመስጠት እየተመዘገበበት ያለውን የሕ/ተ/ም/ቤት እና የክልል ም/ቤት የምርጫ ክልሎች ያሳያል።

- ○ ወደታች የሚከፈተው ሜኑ (ድሮፕዳውን ሜኑ) ውስጥ የምርጫ ጣቢያን ይምረጡ – ከቋሚ የመኖሪያ አድራሻዎ አቅራቢያ የሚገኘው የምርጫ ጣቢያ ስም በትክክል የትኛው እንደሆነ ለማወቅ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል ጽ/ቤት፣ ዘመዶችዎንና ጎረቤቶችዎን ጠይቀው መረዳትዎን ያረጋግጡ (ወደታች የሚከፈተው ሜኑ ውስጥ የሚገኘው የምርጫ ክልሎች ዝርዝር የተመሰረተው በቋሚ አድራሻ፣ ማለትም ተማሪው ድምፁን በሚሰጥበት የምርጫ ክልል ላይ ሲሆን፣ የምርጫ ክልሉን ስም የሚይዝም ይሆናል)

- ○ ነባር የአካል ጉዳት ካለብዎ፣ አካል ጉዳተኝነትን የሚመለከተው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ

- ○ የተማሪውን የመታወቂያ ካርድ ሶፍት ኮፒ ይጫኑ – የተማሪ መታወቂያ ካርድዎን ስካን አድርገው ወይም በትክክል ፎቶ አንስተው ለመጫን ዝግጁ ማድረግዎትን ያረጋግጡ



የመራጮች ምዝገባን በመሙላት







ደረጃ 4 – የመረጃን ትክክለኛነት ማረጋገጥ

አስፈላጊ መረጃዎችን ካስገቡና የተማሪ መታወቂያ ካርድዎን ከጫኑ በኋላ፣ ያስገቡት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ያጣሩ። የአጻጻፍ ግድፈት ወይም ስህተት መፈጠሩን ካስተዋሉ፣ “በመራጭነት ይመዝገቡ” የሚለውን ለምንካትዎ በፊት ስህተቱን ያርሙ።

ደረጃ 5 – የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀት ሕትመት
“በመራጭነት ይመዝገቡ”” የሚለውን ጠቅ ካደረጉ በኋላ፣ ስርዓቱ የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ለሕትመት ዝግጁ በሆነ በ pdf መልክ ያሳያል። “አትም” የሚለውን ጠቅ በማድረግ የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ማተም ይችላሉ።

**በተጨማሪም፣ የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀቱ እርስዎ አካውንት ወደከፈቱበት የኢሜይል አድራሻም ይላካል፤ እንደዚሁም፣ ከድምፅ መስጫ ቀን በፊትና በዕለቱ ወደ አካውንትዎ ገብተው በማንኛውም ጊዜ ሊያትሙት ይችላሉ።**

**ጠቃሚ፡** በድምፅ መስጫው ዕለት በምርጫ ጣቢያው የእርስዎ ድምፅ ለመስጠት ብቁነት እስከሚረጋገጥ ድረስ ኦንላይን የመራጮች ምዝገባ በጊዜያዊነት ነው የሚያገለግለው። ድምጽ ለመስጠት የሚከተሉትን ይዘው መቅረብዎን ያረጋግጡ፡

1. የመራጮች ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣
2. የተማሪ መታወቂያ ካርድ እና
3. ድምፅ ለመስጠት በተመዘገቡበት የምርጫ ክልል ውስጥ ቢያንስ ለ6 ወራት መኖርዎትን የሚያረጋግጥ ሰነድ።

በምርጫ ክልሉ ውስጥ ለ6 ወራት መኖርዎትን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከሌለ፣ ይህንኑ የሚያረጋግጡልዎ ሶስት ምስክሮችን ያቅርቡ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ